ፓኖራማ ቁጥር 71

**የትዝብት አድማስ**

ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓም

## <u>የጋራ ግብ የሌለው ተቃዋሚ ፥ የአምባገነን ሥርዓት መጫወቻ ይሆናል</u>

ጤናማ ጭንቅላት ኖሮት በሰላ አዕምሮ የታደለ ማነኛውም አትዮጵያዊት/ዊ ዜጋ ሀገሩ አሁን ያለችበትን ሁኔታ በትክክል ሊረዳ አይችልም ማለት የሚቻል አይደለም።እንዲያውም ለዕለት የሚልሰው-የሚቀመስው ከሌለው ድሃ ዜጋ አንስቶ ፥ ቁንጣን ይዞት አልጋው ላይ እስከ ሚገላበጠው ከርስ- አደር ድረስ የሀገሩን ወቅታዊ ይዞታ በትክክል እንደሚገነዘበው መጠራጠር አይቻልም ። በነኝህ ሁለት ዓይነት ዜጎች መካከል በርካታ ልዩነቶች ሊኖሩ ቢችሉም፥ በአንድ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ግን የሚስማሙ እንደሆነ ይታመናል ። ወያኔ ለኢትዮጵያ መርገም መሆኑን ሆዳሞቹም የሚስቱት አይደለም ። ከርሳቸው ቀድሞባቸው ነው እንጂ ። ስለ ወያኔ ዓላማ ፥ ድርጊት ፥ ባኅርይና ሁለንተናዊ ማንነት ተደጋግሞ-ተደጋግሞ የተነገረ ፥የተገለፀና የታወቀ በመሆኑ ያንኑ ሀቅ ቢደግሙት ቢሰልሱት ጉንጭ-አልፋ ከመሆን አይዘልም። ወያኔዎቹ የሚሰሩት ሁሉ ፀሀይ የሞቀው ሀገር ያወቀው በመሆኑ ወያኔን እናጋልጥ ብሎ መዳከር ትርፉ ውሃ መውቀጥ ከሆነ ቆይቷል ። ይህ ማለት ግን መለስና ኩባንያው በየወቅቱ የሚፈፅሙትን ብሔራዊ ወንጀል በቅርብ እየተከታተሉ ለሕዝብ የማሳወቁ ተግባር ይቆማል ማለት አይደለም ። የወያኔዎቹን እኩይ ተግባር ፥ እየተከታተሉ ማወቅና ለሕዝብ ማሳወቅ ከትግላችን አንዱ ክፍል ስለሆነ ያንን ከማድረግ ወደኋላ አንልም ። ይህንንም ወያኔ በሚገባ በማወቁ ነው፥ " ኢሕአፓን ካላጠፋሁ ሰላም አላገኝም " በሚል ሥነ-አዕምሮ የሚዳክረው ። ኢሕአፓ ደግሞ ፥እንኳንስ ከተፎከረ፥ ከተወረወረ አምልጦ እራሱን መከላከል ብቻ ሳይሆን፥ በኢትዮጵያ ጠላቶች ከርሰ- መቃብር ቆም የመታገል ልምድ ስለገበየ ፥ የነመለስ ዜናዊን ድንፋታ ከመጤፍ የሚቆጥር ፓርቲ ሆኖ አልተገኘም ። ጉዳዩ ግን ይኸ አይደለም ።

የተቃዋሚው ጎራ የጋራ የሆነ ብሔራዊ ዓላማ በአለመያዙ ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ያደረገው ጥረት ሁሉ ያመረቃ ውጤት ሳያስመዘግብ ቀርቷል። በተለያዩ ጊዜያት የተጣሩት በጋራ የመስራትና ኅብረት የመፍጠር ሙከራዎችም የውሃ ሽታ እየሆኑ አልፈዋል ። ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት ( ኢዴኃቅ) ጀምሮ ፓሪስ አንድ፥ ፓሪስ ሁለት ፥ የኢትዮጵያ ተቀዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት ( ኢተፖድኅ) የኢትዮጵያ ተቀዋሚ አማራጭ ኃይሎች ፥ እስከ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ( የኢዴኃኅ) ድረስ ይህ ነው የማይባል ጥረትና ድካም ተደርጓል ። እልህ አስጨራሽ መሰናክሎች ታልፈዋል ። ከጥንስሱ ጀምሮ እስከ ምስረታዎቹ ድረስ በየወቅቱ የተከሰቱትን ሰርጎ ገቦችና የወያኔን ሰላዮች በሙሉ ተከታትሎ በመድረስ፥ ከሞላ ጎደል የኅብረት ሙከራዎቹን ለማዳን ተችሎም ነበር ። ይህ ማለት ግን ፈጽሞ ንቅናቄዎቹ ሁሉ ከወያኔ ሰላይች የጸዱ ነበሩ ማለት አይደለም።ይም ሊያስገርም የሚችል ክስተት አልነበረም። ወደፊትም ሰላዮችና ሰርጎ ገቦች በተለያየ መልክና ቅርፅ ሊመጡ አይችሉም ማለት አይቻልም ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የተጠላና የተወገዘ ሕዳጣን ቡድን ፥ የደህንነቱ ማረጋገጫ ሰላዮችና ሰርጎ-ገቦች ስለሆኑ የስለላውን ተግባር ማጠናከርና የሰርጎ-ገቦችን ስምሪት ለማስፋት ተግቶ ይሰራ በታል። የተቃዋሚ ክፍሎች እንደ የድርጅቶቻቸው ጥንካሬ ፥ይዘት፥ ተመክሮና ታሪክ ወያኔ እየገመገመና እየተከታተለ ሰርስሮ በመግባት በማዳከምና በመቆጣጠር የገበጣ ጨዋታውን ከሞላ ጎዳል አያካሂድም ለማለት የሚቻል አይደለም ። ይህ ሁኔታ ሊከሰት የቻለው ፥ በወያኔዎቹ ችሎታና ትጋት ሳይሆን ፥ በአብላጫው በተቃዋሚ ጎራ አንድነት ማጣትና ከሁሉም በላይ ደግሞ የጋራ የሆነ ብሔራዊ ራዕይና ግብ ሊኖረው ስለአልቻለ ነው። የሀገርን ጥቅም እያስቀደሙ የየግል ድርጅትንና መሪዎችን ምኞት በሁለተኛ ደረጃ እስካላስቀመጡ ድረስ፥ በኢትዮጵያ የተቃዋሚዎች ድርጅቶች መካከል የጋራ ብሔራዊ ራዕይና ዓላማ የበላይነት አግኝቶ የጠነከረ ኃይል በመፍጠር ወያኔን ለመቋቋም ያዳግተዋል ። ይህ ተስፋ አስቆራጭ አባባል መስሎ ሊታይ ቢችልም ፥ የሆነውን ታሪክ በትክክል ገምግሞና ተገንዝቦ ከዚህም ስህተት ተምሮ የተሻለ ሁኔታን አመቻችቶ ወያኔን ለማርበትበት የሚያስችለሉትን መሰናዶዎች ማድረግ አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን ለመናገር ነው ። የኢትዮጵያ ወቅታዊው ሁኔታ ፥ ባለፈው ድክመትና ችግር ላይ ብቻ ማተኮረን ሳይሆን ፥ ወደፊት ምን መደረግ ይኖርበታል ? ወደሚለው አቅጣጫ ሰጭ አጀንዳ ማተኮርን ይፈልጋል ። ይጠይቃል ። በተቃዋሚው ጎራ እስካሁን ስለታየው ድክመት ማነው ምክንያት የሆነው? ወደሚለው ወደ እርስ -በእርስ ጣት መጠቋቆምና ፋይዳ-ቢስ መወነጃጀል ከመረባረብና ወደ አጥፊና ጠፊ ጉድጓድ ለመግባት ከመሽቀዳደም ይልቅ ፥ በዳይም እኛ ፥ ተበዳይም እኛ ብሎ ፥ያለፈውን ፀገም ወደኋላ በመተው ለአዲስ ራዕይና ብሩኅ ተስፋ መረባረብ ሀገሪቱን የሚያድናት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ይህ ካልሆነ ፥በአፄው ዘመን እንደነበረው ፓርላማ አባላ

“ እኔማ ይህንን አስመዝግቤ ነበር  የሚሰማኝ  አጥቼ  ነው እንጅ  ” ቢሉት  ኋላ  ከታሪክ ፍርድና ከትውልድ ወቀሳ አያድንም ፡፡

የአምባገነን ሥርዓት ከሁሉም በላይ የሚያረካው ፥ የተቃዋሚ ክፍል መዳከምና መበታተን ለመሆኑ ምሥጢር አይደለም  ፡፡ ይህን  ካረጋገጠ  ደግሞ ፥ እርሱ  በሚያመቸው  መንገድ የፖለቲካ ዳማ ወይም ገበጣ  ጨዋታውን በሰከነ መንገድ ሳይሆን በተረበሸ መንፈስ እያካሄደ ሥልጣኑን በይበልጥ የሚያጠነክርበት አመች ጊዜ ያገኘ ይመስለዋል ፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት የተቃዋሚው ጎራ ሊኖረው የሚችለው ምርጫ ሁለት ብቻ ይሆናል ፡፡  አንደኛውና የሚደገፈውም ፥ካለፈው ስህተቱ በመማር ተሰባስቦ ኀብረቱን አጥንክሮ ለታሪክና ለትውልድ የሚጠቅም  ተግባር ለመስራት የማይቀረውን  መስዋዕት እየከፈሉ መታገል ነው ፡፡ ሁለተኛው ምርጫ ፤ እየተገዙ “ መታገል” በሚለው  የአጎብዳጆችና የተስፋ  ቢሶች መመሪያ እየተደናበሩና  ወያኔንም  አቤት  ወዴት ብሎ   እየተገዙ  መኖር ነው  ፡፡  መኖር ከተባለ ማለታችን ነው ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችንና ዜጎቿ  ፥ የመጀመሪያውን   ምርጫ   እስከመጨረሻው  አንግበው ፥ በዓላማቸው  ፀንተው  ወያኔን  አምርረው   የሚታገሉላቸው  በትግል  የተፈተኑ  ታጋዮች ስለአሏቸው ፤ሁኔታው እንደዚህ እንደሆነ እንደማይቀጥል ያምናሉ ፡፡የአምበገነኖች ድንፋታ የተመሠረተው በውጭ  ኃይሎች  ርዳታ መሆኑን ስለሚያውቁ፥ የውጭ ርዳታ ደግሞ የሚያጠነጥነው ያው በራሱ የግል ጥቅም ዙሪያ ስለሆነ ፥ ዞሮ ዞሮ የመጨረሻው አቸናፊ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡  ይህ  ማለት  ግን   ለወያኔ የሚለገስለት የውጭ ርዳታ  እስኪነጥፍ ድረስ ሀገሪቱ በነመለስ ዜናዊ ከመጥፋት ትድናለች ማለት አይደለም ፡፡ ሌላው እንኳን ባይሳካለት፥ ወያኔ  ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የሚያሰኟትን ብዙዎችን ተቋማትንና ሀገራዊ መሠረቶችን ማዳከሙንና ማጥፋቱን ይቀጥልበታል ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለዘመናት የቆዩትን ታላላቅና  ነባር  ሃይማኖቶችን  እያዳከመና እያጠፋ፥ በባዕዳን ዕምነቶችና በርካሽ ባኅሎች መተካት ይገኙባቸዋል ፡፡ ብሔራዊ ዕሴቶችን እያወደመ በጎጥና በመንደር ጠባብ አመለካከት መለወጥ ፥ ኢትዮጵያ  የምትባል  ሀገር  ከአንድ  መቶ ዓመት በፊት ያልነበረች ነች ለሚለው ቢከፍቱትተልባ ለሆነው አቋሙ ማጠየቂያ የሚረዳው ይመስለዋል፡፡   በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሀገራዊ  ስሜት  ታንፀው  ሊያድጉ  የሚገባቸውን የሀገሪቱን ህፃናት በጠበበና በመከነ የዘረኛ አዕምሮ  ተበክለው እንዲያድጉ  በዕቅድ መስራት ነገ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንዳትኖር ከሚያደርገው ዕኩይ አቅዱ ጋር  የተየያዘ ነው ፡፡ ይህም አሁን ባለው  የመልክዐ-ምድር ክልል ፥  ፈጥሮ ሊያት   የሚመኛትን  የታላቂቷን ትግራይን

ልዕለ-ኃያልነት ዋስትና የተረጋገጠ እንዲሆን ካቀደው ዓላማው ጋር ይስማማለታል፡፡ ይህንን ዕኩይ ዕቅዱን በቅርብ እየተከታተሉ ለማክሸፍና ለመቃወም እንዳይችሉ አብዛኛዎቹን ተቃዋሚ ክፍሎች የተባሉትን በራሱ የፖለቲካ መድረክ ዙሪያ እንዲደነሱ የአሻንጉሊት ሚና ፈቅዶላቸዋል፡፡ የማይቆረጠሙ የብረት ቆሎ የሆኑትን አይበገሬ ተቃዋሚዎችን ደግሞ ያለ ኃይሉን በማጠራቀም ሊያጠፋ ይፍጨረጨራል ፡፡ ውሎ አድሮ የማይቀርለትን ዳግማዊ የካቲትን ሕዝባዊ አመፅ በኃይል ለመቋቋም የሚያስችለውን የጦር ኃይል አሰናድቷል ፡፡ ከመስመር መኮንኖች ጀምሮ እስከ ሻምበል አዛዦች ደረጃ ያለውን አካትቶ ፥ ከዚያም ከፍተኛ ጄኔራል መኮንኖች የሚቆጣጠሩትና የሚያዝዙት የወታደር መዋቅር የተገነባው በትግራይ ተወላጆች ማለትም የወያኔ ሎሌዎች ብቻ እንደሆነ ያገጠጠ-ያፈጠጠ ሀቅ ሆኗል፡ ከልዩ ልዩ ብሄር ብሄረሰቦች መጥተው የተቀጠሩት ተራ ወታደሮች ግን የተዘጋጁት ከመድፉ አፍ የሚተፋውን የእሳተ ገሞራ ነበልባል ሰለባ ለመሆን ብቻ ነው ፡፡ የመጨረሻ የወያኔ ዓላማም የጥቅሙ ተካፋይና ተሳታፊ ያልሆነውን ተራ ተወጊ ወታደር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ደም ለማቃባት እንደሆነ ጣቱን ከሚጠባ ህፃን በስተቀር መነኛውም ዜጋ በትክክል ያውቀዋል ፡፡የወያኔ የስለላ ድርጅትአወቃቀር፥ የመረቡ ሰንሰለት ጉንጉን፥ የአባላቱ ይዘት ፥ በእየርከኑ የተመደቡት የዕዝና የቁጥጥር ሹማምንት ሁሉ ያው ከአንድ ብሔር የመጡ ናቸው ፡፡ የወያኔ የስለላ መረብ ፥ ከሌሎች ሀገሮች የስለላ ድርጅቶች የሚለየው በርካታ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ፥ ነደያንንና አካለ- ስንኩላንን ሳይቀር የእጅ ቴሌፎን በማደል አስማርቶ እንደሚጠቀምባቸው ግን ሌላው ቢቀር ፥ ለአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ የተሸሸገ አይደለም ፡፡ ይህ ድርጊቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማይቀረው ፍልሚያ ምን ያህል እንደተዘጋጀና የኋላ-ኋላ ወደ አጥፊና ጠፊ ደረጃ በሚሸጋገርበት ወቅት እስካሁን ሲቀብር የቆየውን ፈንጅ ፥ የት ? መቸና ? ማንስ ? እንደሚያፈነዳው በማዕከላዊ- ዕዝና- ቁጥጥር የሚከታተል ምሥጥራዊ ቡድን መኖሩን ሊዘነጋ አይገባውም ፡፡ የወያኔ ባለሥልጣናት የሀገሪቱን የገንዘብና የንግድ አውታሮችን በመቆጣጠራቸው ምክንያት ፥ ያሻቸውን ለማድረግ የሚያስችላቸው የገንዘብ ኃይል አላቸው ፡፡ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ያረረበት ዜጋ በብዛት በሚኖርበት ሀገር ደግሞ ለስለላ ሥራ የሚያገለግሉ ሰዎችን በገንዘብ ለመግዛት ከባድ አይሆንም፡፡ ይህ ግን ወያኔን ከማይቀረው ውድቀቱ አያድነውም፡፡

የመለስ አገዛዝ ወደ ውድቀቱ እያመራ ነው፡፡ ይህ ሀቅ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ውድቀቱ ግን ነገ ይሆን ተነገ ወዲያ ወሳኙ ታጋዩ ኃይል ነው ፡፡ ሀገር ወዳድ ኃይሎች ተጠናክረው ከታገሉና ህዝብን ሊያደራጁ ከቻሉ ድልን ይቀዳጃሉ ፡፡ ለዚህም ነው የወያኔንና የቅጥረኞቹን ሻጥረና ከፋፋይ ደንቃራዎች ሁሉ አቸንፎ ለፍፁም ፀረ ወያኔ ድል መታገል ያለብን፡፡